# የ ኢሕአፓ አቅጣጫ 1.

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ታህሣስ 4 እና 5/2012 አዲስ አበባ ውስጥ 9 ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሂዷል፡፡ ይህ ጉባኤ የኢሕአፓን ዳግማዊ ልደት ያበሰረ፣ በርካታ የቀድሞ አባላት፣ አዳዲስ ወጣት አባላት፣ እና ደጋፊዎች የተገኙበት ሲሆን፤ ኢሕአፓ ያልተመለሱ ጥያቄዎቹን ሳይዘነጋ ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ በሚመጥን የትግል ስልት ሊታገልና ሊያታግል እንደገና ቃል የገባበት ታላቅ ዕለት ነበር፡፡

ፓርቲው በ1964 ዓ.ም. ጀርመን አገር ውስጥ በመርሀግብሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጥያቄዎችን በማንሳት የትግል አቅጣጫውን ሲቀይስ የሚከተሉትን አንኳር የመፍትሄ ሀሳቦች አቅርቦ ነበር፡

ሀ. መሰረተ ሰፊና ተራማጅ የሆነ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት መመስረት፣ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ማቋቋም፣

ለ. “መሬት ለአራሹ”ን …በስራ ላይ ማዋል፥ ሐ. ከውጭ ተጽዕኖ ነፃ የሆነ ዲሞክራሲያዊና በፕላን የሚመራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባትና የሠፊውን ሕዝብ ማቴሪያላዊና መንፈሳዊ ደህንነት ማሻሻል፣

መ . የብሔሮች እኩልነት ሙሉ በሙሉ ታውቆ ፈቅዶ መዋሃድ በሚባለው መርህ መሰረት የሚገነባውን የመንግስት ዓይነትና ሥርዓት በእኩልነትና በወንድማማችነት… እንዲቋቋም ማድረግ፣

ሠ . በወንዶችና በሴቶች መካከል የእኩልነት መብት ማስከበርና የሴቶችን መብት ማስከበር፣

ረ. ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የትምህርትና የባህል ሥርዓት ማቋቋም፣ ለሠፊው ሕዝብ ግልጋሎት የቆመ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ማካሄድ፣

ሰ. ሙሉ በሙሉ ሠፊው ሕዝብና አገሪቱን የሚያገለግልና የሚጠብቅ ሕዝባዊ ጦር ሠራዊት ማቋቋም፣

ሸ. በሰላም፣ በገለልተኝነትና ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለሶሺያሊዝም ከሚታገሉ መላ ኃይሎች ጋር በመተባበር ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መከተል የሚሉ ናቸው።

### (ዲሞክራሲያ ቅጽ 1፣ ቁ 6፣ ገጽ 2)

በ1967 ዓ.ም. ወደስልጣን የወጣው ወታደራዊው አገዛዝ የነበረው ኢ- ዲሞክራሲያዊ ተፈጥሮ በእነዚህ የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ የህዝብ ወገን ከሆነው ኢህአፓ ጋር እንዲመክር ስላላስቻለው ፓርቲውን በፀረ ህዝብነት ፈርጆ የዕልቂት ድግስ ደገሰለት፡፡

አብዮት ልጆቿን እንድትበላ ተደረገ፤ አንድ ትውልድም በቀይ ሽብር በትር በሽዎች በሚቆጠር አለቀ፡፡ ኢትዮጵያን የፍርሀት ቆፈን አቆራመዳት፤ ትግሉም ተኮላሽቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ለ17 ዓመታት በአምባገነን ሥርዓት ስር ወደቀ። በዚህም ሳቢያ በ17 ዓመታቱ የደርግ ዘመን ከላይ ከተዘረዘሩት የሕዝብ ጉዳዮች ውስጥ የመሬት ለአራሹ አዋጅ ከመታወጁ በስተቀር ሌላ የተገኘ ለውጥ መጥቀስ አልተቻለም፡፡

የመሬት ለአራሹ አዋጅም ቢሆን ገበሬውን ከባላባት ጭሰኛነት አውጥቶ የመንግሥት ጭሰኛ ከማድረግ ሌላ የፈየደው ነገር አልነበረም፡፡ ደርግ ኢሕአፓን ለማጥፋት በመላ ሀገሪቱ በከተሞችና የትጥቅ ትግለ ይካሄድባቸው በነበሩት የገጠር አካባቢዎች ጭምር

ሙሉ ትኩረቱን በማድረጉ እንደ ህ.ወ.ሓ.ት. ያሉት ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶች በባዕዳን እገዛና ትብብር ሊያድጉና ሊጠናከሩ ቻሉ።የሕዝቡ ብሶትም ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ በደርግ ላይ ያለው ጥላቻ ጫፍ በመውጣቱ የተነሳ ሕዝቡ የብሄር ድርጅቶችን ማሸነፍ እስከመቀበል ደረሰ፡፡

በመሆኑም በ 1983 ዓ.ም. ህወሃት/ኢህአዲግ ደርግን በኤርትራው "ሻዓቢያ"፤ የሱዳን ጦርና ሌሎችም ባዕዳን ድጋፍ አሸንፎ ስልጣኑን ያዘ፡፡ ነገር ግን የሕዝብን ጥያቄና ፍላጎት ሳይሆን የራሱን አጀንዳ ይዞ የመጣው ሕወሃት/ኢሕአዲግ ትኩረቱን በዘር ላይ በተመሠረተ ማንነት ላይ በማድረጉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘመናት አስተሳስረው ያቆዩትን ሀረጎች በጣጠሳቸው፡፡ ቀስ በቀስ ለራስ ዘር ብቻ ማሰብ ለሌላው ግዴለሽነትን ከመፍጠር አልፎ የጥላቻ መንፈስን መዝራት ጀመረ፡፡ እነሆ ላለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት የተዘራው የጥላቻ በሽታ ዛሬ ሰንኮፉ የማይነቀል ነቀርሳ እየሆነብን ነው፡፡ እናም ባሳለፍናቸው የሕወሃት/ኢሕአዲግ የአገዛዝ ዓመታት በስተመጀመሪያው የተዘረዘሩት የሕዝብ ጥያቄዎች ሳይመለሱ ከመቅረታቸው በተጨማሪ መሠረታዊ የሆነውን የአብሮነትና የአንድነት እሴታችንን፣ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን ቀማን፡፡

እነሆ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ መፈናቀልና መገዳደል የየዕለቱ ጭንቀታችን ሆነ፤ ጨካኝነት ሁለተኛ ተፈጥሮአችን እስኪመስል ድረስ ወገን በወገኑ ላይ እጁን አንስቶ ኢ ሰብአዊ ተግባር ሲፈጽም ተመለከትን፤ “እውን እኛ እንዲህ ነን?” ብለን ልንጠይቅም ግድ ሆነ፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያችን ወዴት እንደምትሄድ መላው የጠፋባት፣ የሚናገሩ የበዙባትና መደማመጥ ግን የሌለባት፣ መፍትሄው የራቃት ሆና እንደ እውር ድመት የምትደናበርበት ጊዜ ላይ ነን፤ የትኛውን አምነን የትኛውን እንደምንጠራጠር እስኪጠፋን፣ በየዕለቱ የሚደርሱን መረጃዎች “እግዚኦ!” የሚያሰኙ እየሆኑ ነው፡፡ እናም የእያንዳንዱን ዜጋ መሠረታዊ ፍላጎት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንደምትቀጥል እርግጠኛ መሆን ሆነ፡፡ ኢሕአፓ ኢትዮጵያን እንደሀገር የማስቀጠሉ ጉዳይ ለነገ የማይባልና ከሁሉም ነገር መቅደም ያለበት አጀንዳ ነው ብሎ ያምናል፤ ለዚያም ይታገላል።

## 2. መድረሻን ማወቅ

መዳረሻውን በትክክል የማያውቅ በየት እንደሚሄድ አያውቅም፤ መድረስ የተፈለገበትን ቦታ በትክክል ማወቅ ሲቻል ድንብርብሩ ከወጣው ምስቅልቅል መንገድ ውስጥም ቢሆን ወደ መዳረሻው የምትወስደውን ቀጭን መንገድ ማየትና መከተል ይቻላል፡፡ የሚሄድበትን አጥርቶ ያልተነሳ በትርምስምሱ ውስጥ በመባከን በየትናንሹ እንቅፋት በመሰናከል ሲባዝን ይስተዋላል፡፡ ኢሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ መድረሻውን የሚያውቅ ፓርቲ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አሁን በምትገኝበት ትርምስ ውስጥም ሆኖ ትናንት ወደሳላት፣ ዛሬም በቅርብ ርቀት ወደሚመለከታት ኢትዮጵያ ለመሄድ በቁርጠኝነት ይታገላል፡፡ ያች ኢትዮጵያ ደግሞ፡ የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የተጠበቁባት፣ ድህነትን፣ ረሃብንና መታረዝን ከምድሯ ያጠፋች፣ ፍትኀዊነትና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገቷና በልማት ክንዋኔዋ ከሌሎች የዓለም ታላላቅ ሃገሮች አቻ የደረሰች፣ ሰላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ ፍትኅ የተረጋገጠባት ታላቅ ፌደራላዊት ኢትዮጵያ! ነች፡፡ ይህ ፌደራላዊ አስተዳደር ግን በቋንቋና በጎሳ ላይ ብቻ በመመስረት የሚዋቀር ሳይሆን በሌሎች የበለጠ ሳይንሳዊና አካታች በሆኑ መመዘኛዎች አማካይነት የሚዋቀር ፌደራሊዝም ነው፡፡ ለመሆኑ ጤናማ አእምሮ ኖሮት ይህችን ኢትዮጵያ ለማየት የማይፈልግ/የማይመኝ ኢትዮጵያዊነቱን የሚያውቅና ከልቡ የተቀበለ ዜጋ ሊኖር ይችላል? መፈለግና መመኘት ብቻውን ግን በቂ አይደለም፤ ወዴት ለመሄድ እንደምንፈልግ ስንወስን ወደ አሰብነው ቦታ እንዴት እንደምንደርስም ማሰብ እንጀምራለን፡፡ ኢሕአፓ ከላይ ወደተጠቀሰችው ኢትዮጵያ ለመድረስ ልንከተል የሚገባን መንገድ ዛሬ አንድ ብቻ መሆኑን ያምናል፤ ይህም ሰላማዊ ትግል ነው፡፡

## 3. ሰላማዊ ትግል

ኢሕአፓ ወደሚፈልጋት ኢትዮጵያ ለመሄድ የጀመረው ሰላማዊ ትግል ማህበራዊ ዲሞክራሲን (ሶሻያል ዴሞክራሲን)

መመሪያው ያደረገ ነው፡፡ የማህበራዊ ዲሞክራሲ ዋና ዋና ምሰሶዎች ደግሞ ነፃነት፣ እኩልነት/ፍትሀዊነት እና ወንድማማችነት/እህትማማችነት ናቸው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ወደታለመው እድገት እንድትሄድ ኢሕአፓ የሚከተሉት ወደ ተግባር ይለወጡ ዘንድ ሰላማዊ ትግል ያካሂዳል፡

- እነዚህ የዲሞክራሲ ምሰሶዎች እንዲኖሩ በመጀመሪያ ሀገር መኖር ስለሚገባት፤ የኢትዮጵያን ሕልውና ማስጠበቅ፤
- የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱን፣ ክብሩን፣ ነፃነቱንና ፍትህን ሲቀዳጅ ነው የሚፈለገው ሀገራዊ ሠላም ሊገኝ የሚችለው። ስለዚህም እነዚህ የሕዝቡ መብቶች እንዲከበሩለት ያስፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ በኢትዮጵያ ሁኔታ የተፈጠረው ዘረኝነትና ጥላቻም ከስሩ ተነቅሎ እንዲጣል የተጠናከረ የፖለቲካ ትግል ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁሉም በፊት ከርሃብ ነፃ እንዲሆን፣ አብዛኛውን ሕዝብ እያደቀቀ ያለው ድህነት እንዲወገድ ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ ሠርቶአደሮች ልክ እንደ ሀብታሞቹ ሁሉ በሰብአዊነታቸው ብቻ ክብር፣ መብት፣ ነፃነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች በመንከባከብና በመቆጠብም በማልማትና ኢንዱስትሪዎችንም በማስፋፋት ብኩንነትንና ሙስናን በማስወገድ፣ እድሜው ለሥራ የደረሰ ሁሉ ሥራ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- ከበርቴዎች ፋብሪካዎቻቸው እና ሌሎች የሥራ ተቋሞች በመክፈት ሠራተኞችን ቀጥረው እንዲያሠሩ፣ ማለትም የበለጠ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የንብረት ባለቤትነታቸውን ማክበር፤ ከገቢያቸው ግን ተገቢውን ታክስና ቀረጥ እንዲከፍሉ ለማድርውግ ከአድላዊነትና ሙስና የፀዳ የታክስና የቀረጥ ሥርዓት መመሥረት፣
- ኢኮኖሚያዊ ዕድገትንና ልማትን የሚያሳልጡ መሠረተ-ልማቶችን በአስተማማኝ ደረጃ ቅድሚያ ሰጥቶ ማሟላት፤
- አርሶአደሮች የሚያርሱትን መሬት በግል ንብረትነት እንዲይዙ፤ የከተማ ነዋሪዎችም የግል ቤቶችና ንብረቶች እንዲያፈሩ መብታቸው እንዲከበር ማድረግ፣
- ኢሕአፓ ለጭቁኑና ለተበደለው የኅብረተሰብ ክፍል ወገናዊነትን ቢያሳይም ለመላው የሀገሪቱ ሕዝብ መብት እና እኩልነት፣ ለማስገኘትም በሙሉ ልብ ይታገላል፣ 4. ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ኢኮኖሚያዊ
- ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስፈላጊ ሁኔታ እንጅ በራሱ ግብ አይደለም፤ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማህበራዊ እኩልነትና ለፍትሕ ትኩረት መስጠት ይገባዋል፡፡ ይህም ዜጎች ከብሔራዊ ምርት ዕድገቱ ሊያገኙ የሚገባቸውን ድርሻ በማስጠበቅ ይረጋገጣል፡፡
- ኢሕአፓ ለዘላቂ ልማት ይሠራል፤ ይህም ማለት የቀጣዩን ትውልድ ፍላጎቶች ርካታ አደጋ ውስጥ ሳይከቱ የዛሬን ፍላጎት ማርካት ማለት ነው፡፡ የገበያ ኢኮኖሚን ለመጠበቅ እንዲቻል ሀብት መፍጠር፣ መጭውን ትውልድም ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባትን ይጠይቃል ማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚውን በዘላቂነት ለማሳደግ የመንግሥት ወጭዎች በተለይም ትምህርት፣ ጤና፣ መሠረተ ልማት፣ እንዲሁም ምርምርና ጥናት በቂ እና የረጅም ጊዜ መዋዕለ ንዋይ ሊመደብላቸው ይገባል፡፡
- ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ሲታሰብ በሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት ላይ ብቻ ማነጣጠር የተሟላ ስዕል አይሰጥም ምክንያቱም ይህ ልኬት የሚያመለክተው በአጠቃላይ ምን ያህል እንደተመረተ እንጅ ስለሚከተሉት ነገሮች ምንም አይነግረንም፡
    - o ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እንዴት ይከፋፈላል?
    - o ክፍፍሉ ሚዛናዊ ነው ወይንስ አይደለም?
    - o ጥቂቶች ብዙውን ምርት ይውስዱታል ወይንስ ለብዙሀኑ ይደርሳል?
    - o ለክፍፍሉ መመዘኛው ምንድነው?
    - o ክፍፍሉ መሰረት የሚያደርገው ፍላጎትን ነው ወይንስ ማህበራዊ መደብን?

o የየምርቱ አካባቢያዊ ዘለቄታዊነት የቱን ያህል ነው? ለአካባቢ ጥበቃ የሚውል የመዋዕለንዋይ ፈሰስ ይደረጋል?

o ዕድገቱ እንዴት ተገኘ? የሚሄደውስ ወዴት ነው? የረጅም ጊዜ ልማትን ለማረጋገጥ በመሠረተ ልማት፣ በትምህርት፣ በጤና እንዲሁም በጥናትና ምርር ላይ መዋዕለ ንዋይ ይፈሳል?

● የኢሕአፓ የዕድገት እሳቤም ከአጠቃላይ ዕድገት ባሻገር አሳታፊነቱን የሚመለከት፤ ዕድገቱ ለሠራተኛው፣ ለድህው በተልይም በገጠር ለሚኖረው ድሀ ሕዝብ በሚያመጣው ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

## ማህበራዊ

በማህበራዊ ትንተና ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው አበይት ጉዳዮች ትምህርት እና ጤና፣ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነቶች፣ ሥራ አጥነት፣ የወጣቶችና ሴቶች ጉዳይ፣ ወላጅ አልባነትና ጎዳና ተዳዳሪነት፣ የአረጋውያን ሁኔታና ሴተኛ አዳሪነትን የተመለከቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በርካታ ጥናቶችና ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ በማህበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ኋላ ቀር ከሚባሉት አገሮች አንዷ ስትሆን ይህም በጥራት ጉድለትና በዝቅተኛ ተደራሽነት ይገለፃል፡፡

◆ በትምህርት ረገድ የሥርአተ ትምህርት እና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ጥናት እንዲደረግ፣ የሀገር በቀል ዕውቀቶች ትኩረት እንዲሰጣቸው፣ እንዲሁም በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ አንድነትን የሚያመጡ የቋንቋ ፓሊሲዎችን ማውጣትና መተግበር፣

◆ የጤና ሽፋን፣ ተደራሽነትና ፍትሀዊነት እንዲረጋገጥ፣ ብዙሀኑ ህዘብ የንጹኅ ውሀና የጤና አግልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ◆ ለአሰሪዎች በመንግሥት በኩል የሚደረገው ማበረታቻ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሠራተኛው የመደራጀትና ሌሎች መብቶቹ እንዲከበሩ፣ ◆ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እንዲነደፉና ወደተግባር እንዲለወጡ፣

◆ የወጣቶች፣ የሴቶች የህጻናት ተጠቃሚነትና እንክብካቤ ትኩረት እንዲሰጠው፣ ◆ እያንዳንዱ ማህበራዊ አገልግሎት አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ማድረግ ልዩ ትኩረት በሚያሻቸው ቦታ ሁሉ በጥናትና በፖሊሲ የተደገፉ ተግባራትን ማከናወን

◆ ወላጅ አልባ የሆኑ እና ለጎዳና ተዳዳሪነት የተጋለጡ ልጆች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ◆ አረጋውያን በተለያየ መስክ አገራቸውን ሲያገለግሉ መኖራቸውን ታሳቢ በማድረግ የእርጅና ዕድሜያቸውን በመከበርና አስፈላጊ እንክብካቤ በማግኘት እንዲኖሩ ማስቻል

◆ ሴተኛ አዳሪነት የተለያዩ ምክንያቶች የፈጠሩት ማህበራዊ ችግር መሆኑን በመገንዘብ በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ በመሥራት ሴተኛ አዳሪዎች የተሻለ አማራጭ የሥራ መስክ እንዲፈጠርላቸው መሥራት ኢሕአፓ ለእነዚህ ማህበራዊ አገልግሎቶች መሻሻል የሁሉም ዜጋ አስተዋጽኦ እንደሚያስፈልግ ሲያምን መንግሥት ለማህበራዊ አገልግሎቶች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለበት መግለጽ ይወዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ይታገላል።

## መደምደሚያ

ኢሕአፓ የሕዝብ ልጅ ነው! ዛሬም እንደ ትናንቱ በሕዝቡ ውስጥ ያለውን ቦታ ያጠናክራል፤ ሕዝቡን ያዳምጣል፣ ከሕዝቡ ይማራል፤ መልሶም ሕዝቡን ያስተምራል፣ ያደራጃል፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከሴራ እና ከመጠላለፍ የተሻገረ፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተና ከራስ ወዳድነት የላቀ እና ሕዝቡን ያስቀደመ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኢሕአፓ ጋር እንዲቆም፤ በጋራ ጥረታችንም ኢትዮጵያ ከድህነትና ከችግር የተላቀቀች፣ ዲሞክራሲያዊትና ለሁላችንም እኩል የሆነች በፍትሀዊነት የተዋጀች ሉአላዊት አገር እናደርጋት ዘንድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከገቡበት ችግር እስኪላቀቁ ድረስ የኢሕአፓ ትግል ይቀጥላል!**